# SIDAAMU DAGOOMU QOQQOWI MOOTIMMA AFFINI GAAZEEXA

# የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አፍኒ ጋዜጣ

# SIDAAMA NATIONAL REGIONAL STATE AFFINI GAZETA

1ki Diro Kiiro 16

Hawaasa, Dotteessa 15, 2013 M.D

Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Amaalete Mini Allaalshi Hundaanni Fulinoho

በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

፩ኛ ዓመት ቁጥር ፲፮

ሀዋሳ፣ ሚያዝያ ፲፭ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም


**<u>Amado</u>**

**Lallawu Kiiro 16/2013**


**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Shariyu Yoo Minna Uurrisate Fulino Lallawa …………… Qoola ….**


**<u>ማውጫ</u>**

**አዋጅ ቁጥር ፲፮/፳፻፲፫**


**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሸሪዓ ፍ/ቤቶችን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ……….. ገጽ…**


## Lallawu Kiiro 16/2013

## Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Shariyu Yoo Minna Uurrisate Fulino Lallawa

Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Bayriidi Seeri quwa 33 (5) garinni adhammete, hojjinna maatete qoosso aana ka'anno seeru hajubba lainohunni fajjo kaima assinohunni budunna ammanote seerinni yoo afi'rate dandiinanniha ikkinohura;

Qoqqowu Bayriidi Seeri quwa 63 (1) garinni loosu aana nooti mootimmate afamooshshi noonsari ammanotenna budu yoo uurrinsha tantanama dandiitannota seerunni worroonniha ikkinohura;

## አዋጅ ቁጥር ፲፮/፳፻፲፫

## የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሸሪዓ ፍ/ቤቶችን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፴፫(፭) መሠረት የጋብቻ፣ የግልና የቤተሰብ መብት ላይ የሚነሱ የሕግ ጉዳዮችን አስመልክቶ በፈቃደኝነት ላይ በተመሠረተ ሁኔታ በባህላዊና በኃይማኖት ሕጎች ለመዳኘት የሚቻል በመሆኑ፤

በክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፷፫(፩) መሠረት በሥራ ላይ የነበሩና የመንግሥት እውቅና ያላቸው ኃይማኖታዊና ባህላዊ የዳኝነት ተቋማት ሊደራጁ

Qoqqowinkera Shariyu Yoo Minna ikkadimma noo garinni tantanantanno assa hasiissannota ikkitinohura;

Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Amaale Mini Qoqqowu Bayriidi Seeri Quwa 48 cinaancho quwa 3 fidale (a) garinni aane nooha lallamboonni.

## GAFA MITE

## Xaphooma Woro

**1. Harancho Umo**

Konne lallawa “Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Shariyu Yoo Minna Uurrisate Fulino Lallawa Kiiro 16/2013” yine xawisate dandiinanni.

**2. Tiro**

Qaalu horo wole tiro uytannota ikka hoogguro konni lallawi giddo:

1. **“Qoqqowo”** yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowooti.
2. **“Qaadi”** yaa Shariyu Yoo Minnara aye deerrira mootoonsineenna loosanno yooaanchooti.
3. **“Qara Qaadi”** yaa Qoqqowu Xaphoomu Shariyu Yoo Mini albiidi woy gambisaancho Qaadiiti.
4. **“Hundaano”** yaa aliidinna umi dirimi shariyu yoo minna qineesaano ikkite yoonsa minna looso massagganno qaadootaati.
5. “**Qoqqowu Shariyu Yoo Minna”** yaa umi

እንደሚችሉ የተደነገገ በመሆኑ፤

በክልላችን የሸሪዓ ፍ/ቤቶች ብቃት ባለው ሁኔታ እንዲደራጁ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የሲዳማ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት በክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፰ ንዑስ አንቀጽ ፫ ፊደል ተራ (ሀ) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩ አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ “የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሸሪዓ ፍ/ቤቶችን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር ፲፮/፳፻፲፫” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪ ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጥ ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩ **“ክልል”** ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልል ነው፡፡

፪ **“ቃዲ”** ማለት በሸሪዓ ፍ/ቤቶች ውስጥ በየትኛውም ደረጃ ተሹሞ የሚሠራ ዳኛ ነው፡፡

፫ **“ዋና ቃዲ”** ማለት የክልሉ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍ/ቤት የበላይ ወይም ሰብሳቢ ቃዲ ነው፡፡

፬ **“ተጠሪዎች”** ማለት በከፍተኛ እና በመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤት አስተባባሪዎች ሆነው የየፍርድ ቤቶቻቸውን ሥራ የሚመሩ ቃዲዎች ናቸው፡፡

፭ **“የክልል ሸሪዓ ፍ/ቤቶች”** ማለት የመጀመሪያ ደረጃ፣ ከፍተኛ እና ጠቅላይ ሸሪዓ ፍ/ቤቶች

dirimi, aliidinna xaphoomu shariyu yoo minnaati.

6. **“Fitaabeerete Amanyooti Seera”** yaa 1958 fulino fitaabeerete amanyooti seeraati.
7. **“Songo”** yaa qoqqowu yooaanote gashshooti songo uurrisate lallawi kiiro 5/2012 garinni uurritino songooti.

**3. Koo-teemmate Xawishsha**

Konni lallawi giddo mitte koo-teemmanni xawinsoonnihu hasiishshu garinni wole koo-teemmano amadannoho.

## GAFA LAME

## Uurranna Xaphooma Loosu Amuraate

**4. Uurra**

Hundaanchimmansa Qoqqowu Yooaanote Gashshooti Songora ikkitino:

1. Qoqqowu Umi dirimi Shariyu Yoo Mini,
2. Qoqqowu Aliidi Shariyu Yoo Mini,
3. Qoqqowu Xaphoomu Shariyu Yoo Minna konni lallawinni uurritino.

**5. Qara Woro**

1. Qoqqowu Shariyu Yoo Minna konni woroonni noo hajubba aana gutu yooaanchimma biilloonyi hee’rannonsa:
   a) Ayee adhmate, tidhamate, qallawa murate, qaaqquullu awuutaanchimmanna maatete fiixoomi aana ka’anno hajubba lainohunni

ናቸው።

፮ **“የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ”** ማለት በ፲፱፻፶፰ የወጣ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ነው።

፯ **“ጉባዔ”** ማለት በክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፭/፳፻፲፪ መሠረት የተቋቋመ ጉባዔ ነው።

**፫ የጾታ አገላለጽ**

በዚህ አዋጅ ውስጥ በአንድ ፆታ የተገለፀው እንደ አግባብነቱ ሌላውንም ፆታ ያካትታል።

## ክፍል ሁለት

## ስለመቋቋምና አጠቃላይ አሰራር

**፬ መቋቋም**

ተጠሪነታቸው ለክልሉ ዳኞች አስተዳዳር ጉባዔ የሆኑ፡-

፩ የክልል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤት፣
፪ የክልል ከፍተኛ የሸሪዓ ፍ/ቤት፣ እና
፫ የክልል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍ/ቤት በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

**፭ መሠረታዊ ድንጋጌ**

፩ የክልል ሸረዓ ፍ/ቤቶች ከዚህ በታች በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ የወል የዳኝነት ሥልጣን ይኖራቸዋል፡-

ሀ) ማናቸውም የጋብቻ፣ የፍቺ፣ የቀለብ አወሳሰን፣ አካለ መጠን ያልደረሱ ሕፃናት ሞግዚትነትና በቤተሰብ

yekkeeramaano isiliminnu ammano amanyooti garinni yoo afi'rate sumuu yitinoha ikkiro;

b) Woqifete, Sixootu/hibu/, raggete woy nuzaazete hajo lainohunni ragisiisaanchu woy sixoota aannohu woy tanaazazannohu musiliime ikke woy reyhu rey yannara musiliime ikke reynoha ikkiro;

c) Konni cinaanchu quwi fidale (a) nna (b) hunda worroonni hajubba aana shiqqanno qaxxaro kasaara gumula la'annota ikkituro;

2. Konni quwi cinaanchu quwi 1 iima worronni hajubba yekkeeramaano hajonsa Isiliminnu ammano garinni shariyu yoo mine la'antanonsa gede faajjete hasattonsanni doodhite shiqquro calla ikkanno.

## 6. Sumuu Yaa Woy Giwa Gumula

1. Yekkeeramaanotenni mittu hajosi shariyu yoo mine la"amate woxaratto shiqishiro hajo shiqqinohu shariyu yoo mini wolu yekkeeramaanchi yoote mine hajonsa la"amate sumuu yaannoha ikkiro sumuu yiinota qaxxarote dawaro, sumuu yaannokkiha ikkiro giwasi adhe shiqanno gede woshshattote sokka sonkannisi.

2. Konni quwira cinaanchu quwi 1 aana worroonni garinni yoote mini woshshatto garunni iillitannosi gede assinoonni yekkeeramaanchi giwosi woy sumuu yaasi yoote mini rejistiraarewa shiqe buuxisa hoogiro giwo shiqisha hasirinokkihu gede

ተዛምዶ ላይ የሚነሱ ጉዳዮችን አስመልክቶ ተከራካሪዎች በእስልምና ኃይማኖት ሥርዓት ለመዳኘት ፈቅደው ከሆነ፤

ለ) የወቅፍ፤ የስጦታ/ሂባ/፣ የውርስ ወይም የኑዛዜ ጉዳዮችን በተመለከተ አውራሽ ወይም ስጦታ አድራጊ ወይም ተናዛዥ ሙስሊም የሆነ እንደሆነ ወይም ሟች በሞተበት ሰዓት ሙስሊም ሆኖ የሞተ እንደሆነ፤

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) በተገለጹት ጉዳዮች ላይ በሚቀርቡ ክሶች ኪሣራ መወሰንን በተመለከተ፤

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ላይ በተጠቀሱ ጉዳዮች ተከራካሪዎች ጉዳያቸው በእስልምና ኃይማኖት አማካይነት በሸሪዓ ፍ/ቤት እንዲታይላቸው ግልጽ በሆነ ሁኔታ በፍላጎታቸው መርጠው ከቀረቡ ብቻ ይሆናል፡፡

## ፮ ፈቃደኝነትን ወይም ተቃውሞን ስለመወሰን

፩ ከተከራካሪ ወገኖች አንዱ በሸሪዓ ፍ/ቤት ለመዳኘት አቤቱታ ሲያቀርብ ጉዳዩ የቀረበለት የሸሪዓ ፍ/ቤት ሌላው ተከራካሪ ወገን በፍ/ቤት ለመዳኘት ፈቃደኛ ከሆነ ፈቃደኛ መሆኑንና የክሱን መልስ፣ ፈቃደኛ ካልሆነ ደግሞ ተቃውሞውን ይዞ እንዲቀርብ የመጥሪያ ደብዳቤ ይላክለታል፡፡

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ በተገለፀው መሠረት የፍርድ ቤቱ መጠሪያ በአግባቡ እንዲደርሰው የተደረገ ተከራካሪ ወገን

kiirre hajo nookkiwa la’nanni.

3. Yoote minnanni hajonsa la”antanno gede yekkeeramaano bissa mereero faajjetenni sumuu yaa nookkiha ikkiro hajo shiqqinohu shariyu yoo mini ykkeeramaano hajonsa madawanya yoo mine gumulsiisidhanno gede hajo biilloonyu noo madawanya yoo minira saysanno.
4. Konni quwira cinaanchu quwi 3 aana worroonnihu noo gedeenni hee’reenna yekkeeramaano hajonsa yoote mine la’nanninsa gede sumuu yaa hoogguro yoote mini yooaanchimmate baantoonni fulo nooro woxu higanno asse yekkeeramaano geegeessanno.
5. Yekkeeramaano wogane fajjo kaima assatenni Shariyu Yoo Mine la”antanni noo hajo aye korkaatinni Madawanya Yoo Minira woy Madawanya Yoo Mine la”antanni noo hajo Shariyu Yoo Minira soorrineenna la”antanno gede assa didandiinanni.

**7. Shariyu Yoo Minnara Loossanno Seerubba**

1. Qoqqowu Shariyu Yoo Minna hajo la”ate biilloonyinsa deerra kaima assite shiqqinonsa hajubba buuxxannohu Shariyu seeri garinniiti.
2. Shariyu Yoo Minna amaddino hajubba amanyootu garinni massagate dandiisiissannota loosu aana noota fitaabeerete amanyooti seera ha’runsite loossanno.

ተቃውሞውን ወይም ፈቃደኝነቱን ለፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር ቀርቦ ካላረጋገጠ ተቃውሞ ለማቅረብ እንዳልፈለገ ተቆጥሮ ጉዳዩ በሌለበት ይታያል፡፡

፫ በፍርድ ቤቶቹ ለመዳኘት በተከራካሪ ወገኖች መካከል ግልጽ በሆነ መንገድ ስምምነት በሌለ ጊዜ ጉዳዩ የቀረበለት የሸሪዓ ፍ/ቤት ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸው በመደበኛ ፍ/ቤት እንዲያስወስኑ ጉዳዩን ሥልጣን ላለው የክልሉ መደበኛ ፍ/ቤት ያስተላልፋል፡፡

፬ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ተከራካሪዎች ጉዳያቸው ፍ/ቤት እንዲታይላቸው ያልተስማሙ ከሆነ ፍ/ቤቱ ለዳኝነት የተከፈለ ወጪ ካለ ገንዘቡ እንዲመለስ አዞ መዝገቡን ዘግቶ ተከራካሪዎችን ያሰናብታል፡፡

፭ በተከራካሪ ወገኖች ፈቃድ ላይ ተመስርተው በሸሪዓ ፍ/ቤት በመታየት ላይ የሚገኙ ጉዳዮች በማናቸውም ምክንያት ወደ መደበኛው ፍ/ቤት ወይም መደበኛው ፍ/ቤት መታየት ላይ የሚገኙ ጉዳዮችን ወደ ሸሪዓ ፍ/ቤት ተዘዋውረው እንዲታዩ ማድረግ አይቻልም፡፡

**፯ የሸሪዓ ፍ/ቤቶች የሚሠሩባቸው ሕጎች**

፩ የክልል ሸሪዓ ፍ/ቤቶች የሥልጣን ወሰናቸውን መሠረት አድርገው የቀረበላቸውን ጉዳዮች ሲመረምሩ የሸሪዓውን ሕግ መሠረት አድርገው ይዳኛሉ፡፡

፪ የሸሪያ ፍ/ቤቶቹ የያዙዋቸውን ጉዳዮች ሥርዓት ባለው ሁኔታ ለመምራት እንዲያስችላቸው በሥራ ላይ ያሉትን የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጎች ተከትለው ይሰራሉ፡፡

**8. Shiloota Seyaata**

Ayee manchino yoote mini looso ha’rinsanni yannara ayee doogonni shiloota seyaatate looso loosiro mitto agana ikkanno usura woy 500 (onte xibbee) birra ikkanno woxu qorichinni qorichishamanno.

## GAFA SASE

**<u>Qoqqowu Shariyu Yoo Minna Yooaanchimmate Biilloonye</u>**

**9. Xaphoomu Shariyu Yoo Mini Yooaanchimmate Biilloonye**

Qoqqowu Xaphoomu Shariyu Yoo Mini aantino hajubba aana yooaanchimmate biilloonyi hee’rannosi:

1. Aliidi Shariyu Yoo Mini umi deerri hajo la”ate biilloonyinni lae gumulino hajubbara;
2. Aliidi Shariyu Yoo Mini kado macciishshate biilloonyinni uyno aye gumulo aana shiqqanno hajubbara;
3. Konni quwira cinaanchu quwi 1 nna 2 aana worroonniti xaphooma woro noo gedeenni heedheenna:
   a) Mitte hajo mittu aliidi yoo mininni wole aliidi yoo minira soorrineenna la”antanno gede shiqqanno xa’mubba la”ate biilloonyi hee’rannosi;
   b) Shariyu seera lainohunni qoqqowu Shariyu Yoo Mini shilootta mereero seeru tironna fiche hasidhanno hajubba la”ate biilloonyi

**፰ ችሎት ስለመድፈር**

ማንም ሰው የፍርድ ሥራ በሚከናወንበት ጊዜ በማንኛውም ዓይነት መንገድ የችሎት መድፈር ተግባር የፈፀመ እንደሆነ አንድ ወር በሚደርስ እስራት ወይም እስከ ብር ፭፻ (አምስት መቶ) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

## ክፍል ሦስት

**<u>የክልሉ ሸሪዓ ፍ/ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን</u>**

**፱ ጠቅላይ የሸሪዓ ፍ/ቤት የዳኝነት ሥልጣን**

የክልሉ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍ/ቤት በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

፩ ከፍተኛ የሸሪዓ ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣኑ ውሳኔ በሰጠባቸው ጉዳዮች፤

፪ ከፍተኛ የሸሪዓ ፍ/ቤት በይግባኝ ሰሚነት ሥልጣኑ በሰጠው በማንኛውም ውሳኔ የሚቀርቡ ጉዳዮች፤

፫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ የተመለከቱት አጠቃላይ ድንጋጌዎች እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ) አንድ ጉዳይ ከአንድ ከፍተኛ ሸሪዓ ፍ/ቤት ወደ ሌላ ከፍተኛ ሸሪዓ ፍ/ቤት ተዛውሮ እዲታይ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች የማየት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

ለ) የሸሪዓ ሕግን አስመልክቶ በክልሉ ሸሪዓ ፍ/ቤት ችሎቶች መካከል የሕግ ትርጉምና ፍቺ የሚፈልጉ ጉዳዮችን

hee'rannosi.

**10. Aliidi Shariyu Yoo Mini Yooaanchimmate Biilloonye**

1. Woxu bikkinsa 100,000 (mittu xibbi kumi) birri ale ikkitanno hajubba aana umi dirimi yooaanchimmate biilloonyi hee'rannosi.
2. Umi Dirimi Shariyu Yoo Mini uyno gumulo kadotenni la"ate biilloonyi hee'rannosi.
3. Mitte hajo mittu umi dirimi Shariyu Yoo Mininni wole umi dirimi Shariyu Yoo Minira woy aliidi yoo miniwa soorrineenna la"antanno gede shiqqanno hajo la"ate biilloonyi hee'rannosi.

**11. Umi Dirimi Shariyu Yoo Mini Yooaanchimmate Biilloonye**

Umi dirimi shariyu yoo mini hedotenni 100,000 (mittu xibbi kumi) birri geeshsha ikkitanno hajubba woy woxeho soorra dandiinanikki hajubba aana umi deerri yooaate biilloonyi heerannosi.

## GAFA SHOOLE

## Shariyu Yoo Minna Tantanonna Yooaanchimmate Loosu Ha'rinsho

**12. Xaphoomu Shariyu Yoo Mini Yooaanonna Woloota Loosaasine**

1. Mittu qaru qaadichinna mittu layinki qaadichi hattono loosoho hasiissanno qaadootinna rejistiraarootu heedhanosi.

ለማየት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

**፲ ከፍተኛ የሸሪዓ ፍ/ቤት የዳኝነት ሥልጣን**

፩ የገንዘብ ግምታቸው ከብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ) በላይ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ይኖረዋል፡፡
፪ የመጀመሪያ ደረጃ የሸሪዓ ፍ/ቤት የወሰነውን ውሳኔ በይግባኝ የማየት ስልጣን ይኖረዋል፡፡
፫ አንድ ጉዳይ ከአንድ የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤት ወደ ሌላ የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤት ወይም ወደ ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲዛወር የሚቀርብን ጉዳይ ለማየት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

**፲፩ የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤት የዳኝነት ሥልጣን**

የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤት ግምታቸው እስከ ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ) የሚሆኑ ጉዳዮች ወይም ግምታቸው በገንዘብ ሊተመን በማይችሉ ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

## ክፍል አራት

## የሸሪዓ ፍ/ቤቶች አደረጃጀትና የዳኝነት ሥራ አካሄድ

**፲፪ የክልሉ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍ/ቤት ዳኞችና_ሌሎች ሠራተኞት**

፩ የክልሉ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍ/ቤት አንድ ዋና ቃዲና አንድ ምክትል ዋና ቃዲ እንዲሁም ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ቃዲዎችና ሬጅስትራሮች ይኖሩታል፡፡
፪ የክልሉ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍ/ቤት ለሥራው

2. Loosoho hasiissanno irkote loosaasine heedhasira dandiitanno.

**13. Aliidinna Umi dirimi Shariyu Yoo Minna Yooaanonna Woloota Loosaasine**

1. Aliidinna umi dirimi shariyu yoo minna hundaanchimmansa annu annunku yoote minna ikkitanno biillitto, loosoho hasiissanno qaadootinna rejistererooti heedhannosi.
2. Loosoho hasiissanno irkote loosaasine heedhansara dandiitanno.

**14. Qoqqowu Shariyu Yoo Minna Shilootanna Yoo Uytanno Base**

1. Umi driminna aliidi shariyu yoo minna mittu qaadinni massagamanno shilootinni yoo uytanno.
2. Xaphoomu shariyu yoo mini mittu gambisaanchunna lamu qaadoooti somantino shilootinni yoo aanno.
3. Qoqqowu xaphoomunna shariyu yoo mini uurrinshu shilooti base Hawaasi quchumira ikkitanno.
4. Aliidi shariyu yoo mini uurrinshu shilooti base Hawaasi quchumira ikkitanno. Loosu batinyenna gumaamimma kaima assatenni songo ledotenni qooxeessu aliidi shariyu yoo mine tantantara dandiitanno.
5. Qoqqowu giddo owaantete injaanno hattono woradanna quchumma mereerisitanno umi

አስፈላጊ የሆኑ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞት ሊኖሩት ይችላሉ፡፡

**፲፫ ከፍተኛ እና የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤቶች ዳኞችና ሌሎች ሠራተኞች**

፩ ከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤቶች ለየፍርድ ቤቶቹ ተጠሪ የሚሆኑ ተሿሚዎች፣ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ቃዲዎች እና ሬጅስትራሮች ይኖሯቸዋል፡፡

፪ ፍ/ቤቶቹ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞት ሊኖሯቸው ይችላሉ፡፡

**፲፬ የክልሉ ሸሪዓ ፍ/ቤቶች ችሎትና የማስቻያ ስፍራ**

፩ የመጀመሪያ ደረጃ እና ከፍተኛ የሸሪዓ ፍ/ቤት ችሎቶች በአንድ ቃዲ ያስችላሉ፡፡

፪ የጠቅላይ ሸሪዓ ፍ/ቤት ችሎት አንድ ሰብሳቢና ሁለት ቃዲዎች ተሰይመው ያስችላሉ፡፡

፫ የክልሉ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍ/ቤት ማስቻያ ቦታ ሀዋሳ ከተማ ይሆናል፡፡

፬ ከፍተኛ የሸሪዓ ፍ/ቤት ማስቻያ ቦታ ሀዋሳ ከተማ ይሆናል፡፡ የስራውን ስፋት እና ውጤታማነትን መነሻ በማድረግ ጉባኤው ተጨማሪ የአካባቢ ከፍተኛ ሸሪዓ ፍ/ቤት ሊያደራጅ ይችላል፡፡

፭ በክልሉ ውስጥ ለአገልግሎት በሚያመች እንዲሁም ወረዳና ከተማ አስተዳደሮችን የሚያማክሉ የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤቶችን ጉባኤው ያደራጃል፡፡

፮ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ከ፫ እስከ ፭ የተመለከቱ የሸሪዓ ፍ/ቤቶች ከቋሚ ማስቻያ ስፋራቸው ውጭ እንደ አስፈላጊነቱ በተዘዋዋሪ ችሎት አገልግሎት ሊሰጡ

dirimi shariyu yoo minna songo tantantanno.

6. Konni quwi cinaanchu quwi 3 kayise 5 geeshsha xawinsonni shariyu yoo minna uurrinshu shilootinsa base gobbaanni hasishshu garinni doyite shilooti owaante uyitara dandiitanno.

**15. Qoqqowu Shariyu Yoo Minna Loosu Afoo**

1. Qoqqowu Shariyu yoo minna loosu afii Sidaamu Afoo ikkanno.
2. Sidaamu Afoo dandaannokki owaatamaanchira yoote mini afoo tiranno ogeessa gaamannosi.

**16. Dahaawinokki Shilootira Yoo Aa**

1. Qoqqowu shariyu yoo minna dagate dahaabbinokki shilootira yoo uytanno.
2. Konne quwa cinaancho (1) aana worroonnihu heerirono dagate horonna mooraalera, yekkeeramaanote hasatto, hobbaateranna mooraalera yine hajo dahaawino shilootira la’anara dandiinanni.

**17. Qaadootu Shilootunni Ka’anno Gara**

1. Shariyu yoo mini qaadi shilootunni ka’’ano gede yekkeeramaano bissubba giddonni mittu yoote minira ku’laato shiqisha dandiitanno.
2. Mittu qaadi konni woroonni xawinsoonni hajubba giddo mittetenni shilootunni ka”anno:

   a) Yekkeeramaano bisubba giddo mittu ledo woy seeru ayyaayyamaanchi ledo maalu

ይችላሉ፡፡

**፲፭ የክልሉ ሸሪዓ ፍ/ቤቶች የሥራ ቋንቋ**

፩ የክልሉ ሸሪዓ ፍ/ቤቶች የሥራ ቋንቋ ሲዳሙ አፎ ይሆናል፡፡

፪ ሲዳሙ አፎ ለማይችል ባለጉዳይ ፍ/ቤቱ አስተርጓሚ ይመድብለታል፡፡

**፲፮ በግልጽ ችሎት ስለማስቻል**

፩ የክልሉ ሸሪዓ ፍ/ቤቶች ለሕዝብ ግልፅ በሆነ ሁኔታ ያስችላሉ፡፡

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከተው ቢኖርም ለሕዝብ ጥቅምና ሞራል፣ ለተከራካሪ ወገኖች ፍላጎት፣ ደህንነትና ሞራል ሲባል ጉዳዮች በዝግ ችሎት ሊታዩ ይችላሉ፡፡

**፲፯ ቃዲዎች ከችሎት ስለሚነሱበት ሁኔታ**

፩ የሸሪዓ ፍ/ቤት ቃዲ ከችሎት እንዲነሳ ከተከራካሪ ወገኖች አንዱ ለፍ/ቤቱ ማመልከቻ ማቅረብ ይችላል፡፡

፪ አንድ ቃዲ ከዚህ በታች ከተገለጹ ጉዳዮች በአንዱ ከችሎት ይነሳል፡-

   ሀ) ከተከራካሪ ወገኖች ውስጥ ከአንዱ ጋር ወይም ከጠበቃው ጋር የሥጋ ዝምድና ካለው፤

   ለ) ከተከራካሪዎቹ ውሰጥ ለአንደኛው ወገን አሳዳጊ፣ ነገረ ፈጅ ወይም ጠበቃ በሆነበት ጉዳይ ላይ የተነሳ ክርክር ካለ፤

fiixomitte heedhusiro;

b) Yekkeeramaano bisubba giddo mittoho loossinosiha, *negerefeje* woy seeru ayyaayyamaancho ikkino haja aana kaino yekkeero heedhuro;

c) Yekkero ka’ino haja balaxe yooaanchimmatenni woy araarunni lainoha ikkiro,

d) Yekkeeramaanote giddo mittu widi woy ayyaayyamaanchu ledo yoote mine la’nanni hee’noonni hajo noosiha ikkiro,

e) Konni cinaanchu quwi fidale (a)-(d) geeshsha xawinsoonniri gobbaaanni halaalaancho farco diuysiisanno yiisiisannohu baxxino korkaati nooha ikkiro.

3. Konni quwi cinaanchu quwi 2 garinni qaadichu shilootaho ofolla noosikkita afiro korkaata tajete aana xawise shilootunni kae hajo wolu qaadichi la”anno gede hasiissannore assa noosi.

## 18. Qaadichu Shilootunni Ka”anno Gede Woxaratto Shiqisha

1. Yekkeeramaanote giddo mittu widi konni lallawi quwa 17 hunda xawinsoonni korkaatubbanni mittu qaadichi shilootunni ka”a hasiissinositi leeltusiro qaadichu ka”anno gede yoote minira woxaratto shiqisha dandaanno.

ሐ) ክርክር በተነሳበት ጉዳይ ቀደም ሲል በዳኝነት ወይም በእርቅ ያየው ከሆነ፤

መ) ከተከራካሪዎች ውስጥ አንደኛ ወገን ወይም ከጠበቃው ጋር በፍ/ቤት ክርክር እየታየ ያለ ጉዳይ ካለው፤

ሠ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከፊደል ተራ (ሀ) -(መ) ከተገለጹት ውስጥ ጉዳዮች ውጪ ትክክለኛ ፍትህ አያሰጥም የሚያሰኝ ልዩ ምክንያት ካለ፤

፫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሰረት ቃዲው በችሎት ላይ መቀመጥ እንደሌለበት እንዳወቀ ምክንያቱን በመዝገብ ላይ በመግለጽ ከችሎት ተነስቶ ጉዳዩ በሌላ ቃዲ እንዲታይ አስፈላጊ የሆነውን መፈፀም አለበት፡፡

## ፲፰ ቃዲው ከችሎት ላይ እንዲነሳ አቤቱታ ስለማቅረብ

፩ ከተከራካሪዎች ውስጥ አንደኛው ወገን በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፯ ሥር ከተገለፁ ምክንያቶች አንድ ቃዲ ከችሎት ላይ መነሳት እንዳለበት ከታየው ቃዲው እንዲነሳ ለፍ/ቤቱ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡

፪ አቤቱታ የሚቀርበው ክርክሩ ሳይጀምር ቀደም ብሎ ወይም አቤቱታውን ለማቅረብ ምክንያት መኖሩን አመልካች እንዳወቀ ወዲያውኑ መሆን አለበት፡፡

፫ አንድ ቃዲ ችሎቱን የሚመራው ብቻውን ከሆነ ከችሎቱ እንዲነሳ የቀረበለትን አቤቱታ አይቶ ጥያቄውን የሚቀበል ከሆነ ከችሎት ይነሳል፣ ጥያቄውን የማይቀበል ከሆነ ግን

2. Woxaratto shiqqannohu yekkeero hanafukkinni balaxe woy woxaratto shiqishate korkaati noota ku’laanchu afanni hee’re hakkawontenni shiqisha noosi.
3. Mittu qaadichi shiloota massagannohu callichosi ikkiro shilootunni ka”anno gede shiqqino woxaratto lae ku’lato haa’rannoha ikkiro shilootunni ka”anno; ku’laato haa’rannokkiha ikkiro kayinni haa’rannokki korkaata tajete aana xawise woxaratto hattee yoo mine noohu wolu shilootira woy wolu shilooti nookkiro kado macciishshanno yoo minira hajo la”antanno gede saysa hasiissannosi.
4. Shilootunni ka”anno gede qaadichu aana woxaratto shiqqinohu wolootu qaadooti ledo shiloota ha’risanna ikkiro woxaratto shiqqinosi qaadichi nookkiwa gattino qaadooti gumulo uytannoha ikkanno.
5. Konni quwi cinaanchu quwi 3 nna 4 garinni uynanni gumulo goofimarchunnitanna kado shiqqannokkita ikkitanno.

**19. Ikkadu Korkaati Hee’rikkinni Woxaratto Shiqisha Qorichishshannota Ikka**

Ku’laanchu qaadichu shilootunni ka”anno gede woxaratto shiqishinohu ikkadu korkaati hee’risikkinni ikkiro yoote mini woxaratto tuge qoricha 300 (sasu xibbi) birri geeshsha ikkannoha ku’laanchu aana murara dandaanno.

የማይቀበልበትን ምክንያት በመዝገቡ ላይ በመግለጽ አቤቱታውን በዚያው ፍ/ቤት በሚገኝ በሌላ ችሎት ወይም ሌላ ችሎት የሌለ ከሆነ ወይም ይግባኙን ለሚሰማው ፍ/ቤት ጉዳዩ እንዲታይ ማስተላለፍ አለበት፡፡

፬ ከችሎቱ እንዲነሳ በቃዲው ላይ አቤቱታ የቀረበው ከሌሎች ቃዲዎች ጋር ችሎቱን እያካሄደ ከሆነ አቤቱታው የቀረበበት ቃዲ በሌለበት በቀሩት ቃዲዎች ውሳኔ የሚሰጥ ይሆናል፡፡

፭ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ እና ፬ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻና ይግባኝ የማይቀርብበት ይሆናል፡፡

**፲፱ በቂ ምክንያት ሳይኖር አቤቱታ ማቅረብ ቅጣት ስለማስከተሉ**

አመልካቾች ቃዲው ከችሎት ላይ እንዲነሳ አቤቱታ ያቀረበው በቂ ምክንያት ሳይኖረው ከሆነ ፍ/ቤቱ አቤቱታውን ውድቅ አድርጎ ቅጣት እስከ ብር ፫፻ (ሦስት መቶ) ድረስ ሊወስን ይችላል፡፡

**፳ ቃዲ ሆኖ ለመመረጥ የሚያበቁ ሁኔታዎች**

የሚከተሉት ሁኔታዎች የሚያሟላ ማንኛውም የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ነዋሪ ሁሉ የሸሪዓ ፍረድ ቤቶች ቃዲ ሆኖ ሊሾም ይችላል፡፡

፩ በእስልምና ትምህርት ተቋማት በሸሪዓ ሕግ እና በመደበኛ ትምህርት ጉባኤው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ለጠቅላይ፣ ለከፍተኛ እና ለመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤቶች የሚገለጸውን ዝቅተኛ መስፈርት የሚያሟላ፤

**20. Qaade Ikke Dooramate Hasiisannori**

Aante noore wonshannohu ayee Sidaamu Dagoomu Qoqqowi teessaanchi Shariyu Yoo Minnara qaade ikke mootoo'mara dandaanno:

1. Isiliminnu rosu uurrinshara shariyu seerinninna madabanyu rosinni songo fushshitanno biddissi garinni xaphoomu, aliidinna umi dirimi shariyu yoo minnara xawinsanni hoofayidi bikkancho wonshannohu;
2. Jawaantesinninna akatoommesinni danchu su'mi noosihu;
3. Qaade ikke loosate sumuu yaannohu;
4. Dirisi lemiina ontu ale ikkinohu;
5. Jaddote qaxxaro shiqqeennasi yoote mine qorichishaminokkihu woy jaddote rikerde yanna gude sayyamaminohu;
6. Surrete xibbi noosikkihu; nna
7. Qoqqowunniha loosu afoo shoolente dandoonni egenninohu.

**21. Qaadoota Mootoonsinanni Gara**

1. Qoqqowu Isiliminnu hajo aliidi songo Qoqqowu Yooaanote Songonni xa'mo shiqquro qaadoota filtanno.
2. Isilaamu songo gambisaanchi, songotenni shiqinshoonnirenna babbaxxino deerrira gaamantanno gede huurotenni roore irko afidhino feeffata qaadootita harancho heeshshonsa dhagge xawishsha Qoqqowu Yooaanote Gashshooti Songora shiqishanno.
3. Ayee deerrira gaamantanno qaadooti mootoomme Qoqqowu Xaphoomu Yoo Mini

፪ በታታሪነቱና በሥነ-ምግባሩ መልካም ስም ያተረፈ፤

፫ ቃዲ ሆኖ ለመስራት ፈቃደኛ የሆነ፤

፬ ዕድሜው ከ፳፭ ዓመት በላይ የሆነ፤

፭ በወንጀል ተከሶ በፍ/ቤት ያልተቀጣ ወይም የወንጀል ሪከርድ ጊዜውን ጨርሶ የተሰየመ፤

፮ የአዕምሮ በሽታ የሌለበት፤

፯ የክልሉን የሥራ ቋንቋ በአራቱም ክህሎት የሚያውቅ፡፡

**፳፩ የቃዲዎች አሿሿም**

፩ የክልሉ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ጉባዔ ከክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ጥያቄ ሲቀርብለት የቃዲዎችን ምልመላ ያከናውናል፡፡

፪ እስምልና ጉባዔው ሰብሳቢ፣ በጉባዔው የተጠቀሙበትንና በተለያዩ ደረጃ እንዲመደቡ የድምጽ ብልጫ ድጋፍ ያገኙትን የዕጩ ቃዲዎች አጭር የሕይወት ታሪክ መግለጫ አዘጋጅቶ ለክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ያቀርባል፡፡

፫ በየትኛውም ደረጃ የሚመደቡ ቃዲዎች ሹመት በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዝደንት አቅራቢነት በክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ይፀድቃል፡፡

፬ ዋናው ቃዲና የከፍተኛ ሸሪዓ ፍ/ቤት ተጠሪ አንዳቸው በሸሪዓ ፍ/ቤቶች ጉዳይ ወይም የቃዲዎች ጉዳይ ሲታይ በዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ስብሰባ ላይ በአባልነት ይካፈላሉ፡፡

Pirezidaantichi shiqisheenna Qoqqowu Yooaanote Gashshooti Songonni wonsinanni.

4. Qaru qaade woy Aliidi Shariyu Yoo Mini albisaanchi shariyu yoo minna hajo woy qaadootu hajo la’nanni wote Yooaanote Gashshooti Songo gambooshshira miilimmatenni beeqqitanno.

**22. Hi’ra E’nannikki Yooaanchimma**

1. Qaadootu yooaate loosonsa hi’ra eannohu nookkiha loossanno; seerunni ikkinnina wolurinni dimassagantanno;
2. Konni lallawi quwa 23 hunda worroonnihu gobbaanno loosonsa agurtanno gede diassinanninsa.

**23. Qaadootu Loosunni Geegeessantanno Gara**

Ayee qaadichi loosunni geegeessamannohu konni woroonni xawinsoonni korkaatubbanniiti:

1. Umisi fajjonni loososi agurara hasi’riro lame agana balaxe borrotenni qorowo aatenni,
2. Dirisi leyawoo ikkeenna wommetenni fuliro,
3. Disipilinete xe’nenni loosunni geegeessamanno gede gumuliro,
4. Xissote korkaatinni looso garisinni ha’rise diafanno yine gumulliro.

**24. Disipiliinete Gumullanni Gara**

1 Qoqqowu shariyu yoo minna qaadootinna rejistraarootu baatooshshu amanyoote (damooza, horaamishshu baatooshshe) lainohunni loosu ayyirrinye, batinyenna akute

**፳፪ የዳኝነት ነፃነት**

፩ ቃዲዎች ሥራቸውን በነፃነት ያካሂዳሉ፣ በሕግ እንጂ በሌላ አይመሩም፣

፪ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፫ ላይ ከተደነገገው ውጭ ሥራቸውን እንዲለቁ አይደረጉም፡፡

**፳፫ ቃዲዎች ከሥራ ስለሚሰናበቱበት ሁኔታ**

ማንኛውም ቃዲ ከሥራ የሚሰናበተው ከዚህ በታች በተገለጹት ምክንያቶች ነው፡፡

፩ በራሱ ፈቃድ ሥራውን ለመልቀቅ ሲፈልግ ከሁለት ወር በፊት የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት፤

፪ ዕድሜው ፷ ዓመት ሞልቶ በጡረታ ሲገለል፤

፫ በዲስፕሊን ጥፋት እንዲሰናበት ሲወሰን፤

፬ በሕመም ምክንያት ሥራውን በሚገባ መፈጸም አይችልም ተብሎ ሲወሰን፡፡

**፳፬ ስለ ክፍያ ሥርዓት እና ዲሲፕሊን አወሳሰን**

፩ የክልሉ ሸሪዓ ፍ/ቤቶች ቃዲዎች እና ሬጅስትራሮች የክፍያ ሥርዓትን (ደመወዝ፣ ጥቅማ ጥቅም) በሚመለከት የሥራውን ክብደት፣ ብዛትና ባህሪን መሰረት በማድረግ ጉባኤው በሚያወጣ መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡

፪ የክልሉ ሸሪዓ ፍ/ቤቶች ቃዲዎች እና ሬጅስትራሮች ሥነ-ምግባር፣ ዲስፕሊንና አስተዳደርን በሚመለከት የክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም የወጡ ሕጎች እንደ አግባብነታቸው ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

kaima assatenni songo fushshitanno biddisinni murtannoha ikkanno.

2 Qoqqowu shariyu yoo minna qaadootinna rejistraarootu akatoomme, dispiliinenna gashshoote lainohunni qoqqowu yooaanote gashshoote songo uurrisate lallawinna lallawa jeefisate fultino seerubba garummansanni jeefisantanno.

3 Konni quwi cinaanchu quwi 2 worronnihu heerirono qaadootanna rejistraarootа loosunni geegeessa lainohunni songo uyitanno gumulo goofimarchunnita ikkitanno.

4 Konni quwi cinaanchu quwi 3 garinni gaadootunna rejistiraarootu hajo la’antanno woyte qaru qaade songote miila ikke beeqqanno.

## 25. Ittishsha Uynanni Gara

1. Mittu qaadichi loosu aana keeshshasi yooaanchimmate amanyoote xeissannoha ikkiro Qoqqowu Yooaanote Gashshooti Songo gambisaanchi ayee deerrira noo qaadicha loosunni ittisate dandaanno.
2. Songote gambisaanchi ittishsha uyni barrinni hanafe mittu agani giddo hajo songote shiqisha hasiissannosi.

## 26. Bajeette

Qoqqowu shariyu yoo minna bajeette aantino buichonni afi’nannita ikkitanno:

1. Qoqqowu mootimmanni;

2. Wole bu’anni afi’nanni irkonni.

፫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተደነገገው ቢኖርም የቃዲዎችና ሬጅስትራሮች ስንብትን በሚመለከት በጉባኤው የሚሰጥ ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል።

፬ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ መሰረት የቃዲዎች እና ሬጅስትራሮች ጉዳይ በሚታይበት ጊዜ ዋና ቃዲ በጉባኤው በአባልነት የሚሳተፍ ይሆናል።

## ፳፭ እግድ ስለሚሰጥበት ሁኔታ

፩ አንድ ቃዲ ከሥራ ላይ መቆየቱ የዳኝነትን ሥርዓት የሚያፋልስ ሆኖ ሲገኝ የክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ሰብሳቢ በማናቸውም ደረጃ በሚገኘው ቃዲ ከሥራ ላይ ማገድ ይችላል።

፪ የጉባዔው ሰብሳቢ እግድ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ውስጥ ጉዳዩን ለጉባዔው ማቅረብ አለበት።

## ፳፮ በጀት

የክልሉ ሸሪዓ ፍ/በቶች በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የሚገኝ ይሆናል።

፩ ከክልሉ መንግሥት፤

፪ ከሌሎች ምንጮች ከሚገኝ ድጋፍ።

## ክፍል አምስት

## ዋና ቃዲ፣ ምክትል ዋና ቃዲ እና ተጠሪዎች

## ፳፯ ዋናና ምክትል ዋና ቃዲዎች አሿሿም እና ተጠሪነት

## GAFA ONTE

**Qara Qaade, Layinki Qara Qaadenna Hundaano**

**27. Qaranna Layinki Qara Qaadi Mootonsanna Hundaanchimma**

1. Konni lallawi quwa 20 qaadimmate worroonni bikaancho wonshitannonna qoqqowu isiliminnu aliidi amaale mininni qaranna layinki qara qaadimara filantinori songote shiqqe mootoo'mitannoha ikkanno.
2. Qaru qaadi hundaanchimma songoteti.
3. Layinki qaru qaadi hundaanchimma qaru qaadirati.

**28. Qara Qaadi Biilloonyenna Loosu Qeecha**

1. Qaru qaadi Qoqqowu Shariyu Yoo Minna albisaanchiimmatenni massaganno,
2. Konni quwi cinaanchu quwi 1 aana worroonnihu noo gedeenni hee'reenna qaru qaadi:
   a) Deerru deerrunni tantanantannota shariyu yoo minna tantano qixxeesse Qoqqowu Xaphoomu Yoo Mini Pirezidantera shiqishanno; fajjiniro loosu aana hosiisanno.
   b) Qoqqowu Xaphoomu Yoo Mini Pirezidantenni sonkanni qaadoota Qoqqowu Shariyu Yoo Minnara beehe loosiisanno.
   c) Qoqqowu Xaphoomu Yoo Mini Pirezidante

፩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳ ለቃዲነት የተመለከቱ መስፈርቶችን የሚያሟሉና በክልሉ የእስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት ለዋናና ምክትል ዋና ቃዲነት የተመለመሉ ዕጩዎች ለጉባኤው ቀርቦ የሚሾሙ ይሆናል፡፡

፪ የዋና ቃዲ ተጠሪነት ለጉባኤው ይሆናል፡፡

፫ የምክትል ዋና ቃዲ ተጠሪነት ለዋና ቃዲ ይሆናል፡፡

**፳፰ የዋናው ቃዲ ሥልጣንና ተግባር**

፩ ዋናው ቃዲ የክልሉ ሸሪዓ ፍ/ቤቶችን በበላይነት ያስተዳድራል፣

፪ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋናው ቃዲ፡-

ሀ) በየደረጃው የሚደራጁ የሸሪዓ ፍ/ቤቶች መዋቅር አዘጋጅቶ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት ያቀርባል፤ ሲፈቀድለትም በሥራ ላይ ያውላል፡፡

ለ) በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት አማካይነት የሚላኩትን ቃዲዎች በክልሉ ሸሪዓ ፍ/ቤቶች ውስጥ በመደልደል ያሰራል፡፡

ሐ) ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች እንዲቀጠሩለት ይጠይቃል፤ ሲፈቀድለትም ሠራኞችን ይቀጥራል፤ በየስራው ደልድሎ ያሰራል፡፡

፫ የክልሉ ሸሪዓ ፍ/በቶች ስላከናወኗቸው ሥራዎች በየስድስት ወሩ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት ሪፖርት ያቀርባል፡፡

loosoho hasiissanno loosaasine gaamannosi gede xa'manno; fajjinisiro loosaasine loosoho eessanno; loosu loosu garinni beehe loosiisanno.

3. Qoqqowu Shariyu Yoo Minna loossino loossa lewu lewu aganinni Qoqqowu Xaphoomu Yoo Mini Pirezidantichira rippoorte shiqishanno.
4. Shariyu yoo minna mixonna bajeette qixxeesse Qoqqowu Xaphoomu Yoo Mini Pirezidantichira shiqishanno; fajjinisiro loosu aana hosiisanno.
5. Loosu mine riqiwe hasiisanno baycho leellanno; xawishshubba aanno.
6. Umisi kaonni woy shiloottate qaagishshinni woy hajamaasinete xa'monni Qoqqowu shariyu yoo minna mereero qara ikkinohu tirote badooshshi noonsa shariyu seera la'anno hajubba kalaqanturo hajo ontunni ajjannokki qaadooti shilootaho ofolte la'anno gede assara dandaanno. Tenne hajora qoqqowu isliminnu hajubba aliidi amaale mininni riqiwamino mittu ulemi beeqqanno gede assanno.

**29. Layinki Qaru Qaadichi Biilloonyenna Loosu Qeecha**

Layinki Qaru Qaadichi:

1. Qaru qaadichi aannosi hajubba loosanno.
2. Qaru qaadichi hee'rannokki yannara qara qaadicha riqiwe loosanno.

**30. Hundaanote Biilloonyenna Loosu Qeecha**

Aliidinna umi dirimi shariyu yoo minna hundaano:

፬ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶቹን ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት ያቀርባል፣ ሲፈቀድለትም በሥራ ላይ ያውላል፡፡

፭ መሥሪያ ቤቱን በመወከል አስፈላጊ ቦታዎች ላይ ይገኛል፣ መግለጫዎችን ይሰጣል፡፡

፮ በራሱ ተነሳሽነት ወይም በችሎቶች አሳሳቢነት ወይም በባለጉዳዮች ጠያቂነት በክልሉ ሸሪዓ ፍ/በቶች መካከል መሠረታዊ የሆኑ የትርጉም ልዩነት ያለባቸው የሸሪዓውን ሕግ የሚመለከቱ ጉዳዮች ሲነሱ ጉዳዩን ከአምስት ያላነሱ ቃዲዎች ተሰይመው እንዲያዩት ማድረግ ይችላል፡፡ በዚህ ጉዳይ ከክልሉ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ም/ቤት የተወከለ አንድ ኡለማ እንዲሳተፍ ያደርጋል፡፡

**፳፱ የምክትል ዋና ቃዲው ሥልጣንና ተግባር**

ምክትል ዋና ቃዲው፡-

፩ በዋናው ቃዲ የሚመሩለትን ጉዳዮች ያከናውናል፡፡

፪ ዋናው ቃዲ በማይኖርበት ጊዜ ዋናውን ቃዲ ተክቶ ይሠራል፡፡

**፴ የተጠሪዎች ሥልጣንና ተግባር**

የከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ የሸሪዓ ፍ/ቤት ተጠሪዎች፡-

፩ ፍ/ቤቶቻቸውን ይወክላሉ፤

፪ ዋናው ቃዲ በሚሰጠው መመሪያ መሰረት የፍ/ቤቱን ሥራ ይመራሉ፤ ሠራተኞችን ያስተዳድራሉ፤

፫ ስለተከናወኑ ሥራዎች ለዋናው ቃዲ

1. Yoote minnansa riqibbanno.
2. Qaru qaadi aanno biddissi garinni yoote mini looso massagganno; loossaasine gashshitanno.
3. Loonsoonni loossa qaru qaadichira isitaatistikisetenni irkisamino xawishsha hasiishshu garinni yana yanatenni rippoorte shiqishshanno; loosonsa hasiishshu garinni qaru qaadichi ledo amaalamatenni loossanno.
4. Woloota seerunni uynanninsa loossa loossanno.

## GAFA LEE

## Addi Addi Woro

**31. Qoqqowu Shariyu Yoo Minna Gumulonna Hajajo**

1. Ayee deerrira noo Qoqqowu Shariyu Yoo Minna la”ate biilloonyinsa hundaanni noo hajo aana uytanno gumulonna hajajo jeefisiissanno bissa jeefissanno gede hajaja dandiitanno.
2. Shariyu yoo mini hajajo iillitinonsa jeefisiisaano bissano ikkito hojji mannooti hajajote garinni jeefisateno ikko jeefisiisate gadacho noonsa.

**32. Yoote Mine La”antanni Noo Hajubba**

Kuni lallawi wonsamara albaanni Wodiidi Daganna Dagoomi Qoqqowi Mootimma Shariyu Yoo Minnara la”antanni noo hajubba konni lallawira worroonni garinni biilloonyu noo qoqqowu shariyu yoo minira soorrineenna la”antanno.

በስታትስቲክስ የተደገፈ መግለጫና እንደ አስፈላጊነቱ በየጊዜው ሪፖርት ያቀርባሉ፤ስለሥራዎቻቸው እንደአስፈላጊነቱ ከዋናው ቃዲ ጋር በመመካከር ያከናውናሉ፤

፬ ሌሎች በሕግ የሚሰጧቸውን ተግባራት ያከናውናሉ፡፡

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፴፩ የክልሉ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ውሳኔዎችና ትዕዛዞች**

፩ በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የክልሉ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በሥልጣን ክልላቸው በሚሸፈኑ ጉዳዮች ላይ የሚሰጧቸውን ውሳኔዎችና ትዕዛዞች አስፈፃሚ አካሎች እንዲፈጽሙ ለማዘዝ ይችላሉ፡፡

፪ የሸሪዓ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ የደረሳቸው አስፈፃሚ አካላትም ሆኑ ግለሰቦች በትዕዛዙ መሠረት የመፈጸም ሆነ የማስፈጸም ግዴታ አለባቸው፡፡

**፴፪ በፍርድ ቤት ላይ እየታዩ ስላሉ ጉዳዮች**

ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግሥት ሸሪዓ ፍ/ቤቶች እየታዩ ያሉ ጉዳዮች በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ስልጣን ወዳለው ወደ ክልሉ ሸሪዓ ፍ/ቤት ተዛውረው ይታያሉ፡፡

**፴፫ የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ጉዳዩ የሚመለከተው አካል ለአዋጁ ተፈጻሚነት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**33. Halamate Gadacho**

Ayeno hajo la’annonsa bissa konni lallawi jeefishshira halamate gadacho noonsa.

**34. Jeefishshu Nookki Seerinna Assooti**

Konni lallawi wodho ledo kiphi yaano seerinna rosamino assooti konni lallawinni hanqafantino hajubbara jeefishshu dinonsa.

**35. Wodhonna Biddissa Fushshate Biilloonye**

Konne lallawa loosu iima hosiisate hasiisanno wodho Qoqqowu Amaale mini fushshara dandaanno.

Konne lallawanna lallawa jeefisate fultanno wodho jeefisate hasiisanno biddissa songo fushshitara dandiitanno.

**36. Lallawu Loosu Aana Hossanno Yanna**

Koni lallawi Dotteessa 15/2013 M.D hanaffe loosu aana hossanno.

**Hawaasa, Dotteessa 15, 2013 M.D**

**Desta Ledamo**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Pirezidaanticha**

**፴፬ ተፈጻሚነት የሌላ ሕግና አሰራር**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ሕግና ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ ለተሸፈኑ ጉዳዮች ተፈፃሚነት የላቸውም፡፡

**፴፭ ደንብ እና መመሪያን የማውጣት ስልጣን**

፩ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልግ ደንብ የክልሉ ምክር ቤት ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪ ይህን አዋጅ እና አዋጁን ተከትሎ የወጣ ደንብን በስራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልግ መመሪያ ጉባኤው ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፴፮ አዋጁ ሥራ ላይ የሚውልበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከሚያዝያ ፲፭ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ ይውላል፡፡

**ሀዋሳ፣ ሚያዝያ ፲፭ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም**

**ደስታ ሌዳሞ**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት**

**ርዕሰ መስተዳድር**